# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
# The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢረ ሜሮን

### ጥያቄ- ሜሮን ምንድን ነዉ?

ሜሮን ማለት ቅዱስ ቅብዕ ነዉ። «ሜሮን» ቃሉ ግሪክ ሲሆን ትርጉሙም ቅብዕ ማለት ነዉ።

### ጥያቄ- ምስጢረ ሜሮን ማለትስ ምን ማለት ነዉ?

ሜሮን ከጥምቀት በሁዋላ የሚፈጸም ነዉ። ይህም ማለት ተጠማቂዉ ሰዉ ጥምቀት ከተፈጸመለ
ት በሁዋላ ሳይዉል ሳያድር ወዲያዉኑ ጥምቀቱ እንደ ተቀበለ ሜሮን ይቀባል፤ ሜሮን ሲቀባም
ከመንፈስ ቅዱስ መወለዱ ይረጋገጥለታል። ተጠማቂዉ ተጠምቆ ሜሮን መቀባቱ መንፈስ ቅዱ
ስን መቀበሉን ያመለክታል።

### ጥያቄ- ምስጢረ ሜሮን ለምን ከጥምቀት ቀጥሎ እንዲፈጸም ይደረጋል?

ምስጢረ ሜሮን ከምስጢረ ጥምቀት ጋር ተያይዞ እንዲፈጸም የሚደረገዉ፣ ተጠማቂዉ ከዉኃና
ከመንፈስ ቅዱስ መወለዱን ለማረጋገጥ ነዉ። እንደዚሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሓንስ
እጅ ተጠምቆ ወዲያዉ ከዉኃ ሲወጣ፣ መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ማለት በርግብ ተመስ
ሎ ከራሱ ላይ ማረፉ (ማቴ.3፣16 ፤ ዮሐ.1፣32) ፣ ሜሮን ከጥምቀት ቀጥሎ ወዲያዉ መፈጸም
ያለበት መሆኑን ያመለክታል፤ ስለዚህ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሥርዓት መሠረት ምስጢረ ጥምቀት
፣ ምስጢረ ሜሮን ፣ ምስጢረ ቁርባን ያለመለያየት በተከታታይ በአንድ ቀን የሚፈጸሙ ምስ
ጢራት ናቸዉ። ይኸዉም ተጠማቂዉ ሰዉ በካህኑ እጅ እንደተጠመቀ፣ ወዲያዉ ሜሮን ይቀባ
ል ሳይዉል ሳያድርም ቅዱስ ቁርባን ይቀበላል ማለት ነዉ። ይህ ቅዱስ ሥርዓት ከዘመነ ሐዋር
ያት ጀምሮ ሲያያዝ የመጣ ነዉና ሊለዉጡት አይገባም።

በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በዉኃ ተጠምቆ ወዲያዉ ሜሮን መቀባት፣ መንፈስ ቅዱ
ስን የመቀበል ምልክት መሆኑን በርከት ያሉ የቤተክርስቲያን ሊቃዉንት በየድርሳናቸዉ አረጋግ
ጠዋል። ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ በማቴዎስ ወንጌል ምዕ.6፣17-18 ያለዉን ኀይለ ቃል ሲተረጉ
ም «ኃጢአትህን በጥምቀት እጠብ፣ ራስህን በቅዱስ ሜሮን ተቀባ፤ እንዲህ ካደረግህ በክርስቶ
ስ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ተካፋይ ትሆናለህ» ሲል አስረድቶአል። ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ
ም ስለዚሁ ሲያስረዳ «በጥምቀት ጊዜ ሜሮን መቀባታችን መንፈስ ቅዱስን የመቀበላችን ምልክ
ት ነዉ ብሎአል። አርባ ስምንተኛዉ የሎዶቂያቀኖናም ስለ ሜሮን ሲገልጽ «የክርስቶስ መንግ
ሥት ወራሾች መሆናችን የሚታወቀዉ ተጠምቀን ሜሮን ስንቀባ ነዉ» ይላል፤ ስለዚህ በጥምቀ
ት ጊዜ ሜሮን መቀባት ማለት መንፈስ ቅዱስን መቀበል ማለት መሆኑን መረዳት ይገባል።

በጥምቀት ጊዜ ቅብዓ ሜሮን መቀባታችንን አስመልክቶ ሐዋርያዉ ቅዱስ ዮሐንስ ሲጽፍ «እናን
ተስ ሁሉን ታዉቁ ዘንድ ከመንፈስ ቅዱስ ቅብዓት ተቀብላችኋል» ሲል አስተምሮአል (1ኛ
ዮሐ. 2፣20)። ቀጥሎም ይህ ቅዱስ አባት «እናንተስ ከእርሱ (ከእግዚአብሔር አብ) የተቀበላች
ሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል። ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም፤ ነገር ግን የእርሱ
መንፈስ እንደሚያስተምራችሁ ዕወቁ....» ማለቱ ነዉ (1ኛ ዮሐ. 2፣27)።

### ጥያቄ- የምስጢረ ሜሮን ምሳሌ የተጀመረዉ መቼ ነዉ?

የምስጢረ ሜሮን ምሳሌ የተጀመረዉ በዘመነ ብሉይ ነዉ። ምሳሌዉም «ቅብዓ ቅዱስ ተብሎ
በመጠራት ለተቀደሰ አገልግሎት መዋል የጀመረዉ በሙሴ ጊዜ ነዉ (ዘጸ.30፣22-25)።

### ጥያቄ- በዘመነ ብሉይ የተቀደሰዉ ቅብዕ ለምን አገልግሎት ይዉል ነበር?

1ኛ/ አሮንና ልጆቹ ቅብዓ ቅዱስ ተቀብተዉ፣ ስልጣነ ክህነትን ተቀብለዋል (ተክነዋል)፤

2ኛ/ በደብተራ ኦሪት (በአገልግሎት ድንኳን) ዉስጥ ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሚዉሉ የቤተ መቅደስ ንዋያት (ዕቃዎች) በሙሉ በተቀደሰዉ ቅብአ ተቀብተዉ፣ ንዋያተ ቅዱሳት ተብለዉ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ይዉሉ ነበር፤

3ኛ/ የእስራኤል ነገሥታትና ካህናት የተቀደሰዉን ቅብዕ (ዘይት) እየተቀቡ ነገሥታቱ ሥልጣነ መንግሥትን እጅ ሲያደርጉ፣ ካህናቱ ደግሞ ሀብተ ክህነትን ይቀበሉት ነበር (1ኛ ሳሙ.10፣1፤ 16፣13፤ 1ኛ ነገሥ. 19፤15-21፤ ዘሌ.8፣12)።

## ጥያቄ- ሜሮን ለምን አገልግሎት ይዉላል?

1ኛ/ በቤተክርስቲያን የክርስቶስ ሥጋና ደም ማቅረቢያ ይሆኑ ዘንድ አዳዲስ ዕቃዎች ማለት ጻሕል፣ ጽዋ፣ ጽርፈ መስቀል፣ መሶበ ወርቅ በጸሎተ ሜሮን ተቀብተዉ ይከብራሉ (የተቀደሱ ይሆናሉ)።

2ኛ/ አዲስ ሕንጻ ቤተክርስቲያን ታንጾ ሲያበቃለት፣ በጸሎት ተባርኮ ቅብዓ ሜሮን ይቀባል፤

3ኛ/ አዲስ ታቦትና አዲስ መንበረ ታቦት ቅብዓተ ሜሮን ተቀብተዉ ይከብራሉ (የተቀደሱ ይሆናሉ)።

4ኛ/ ሜሮን የጸጋን ልጅነት የሚያሰጥ ምስጢር ስለሆነ በጥምቀት ጊዜ «በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም» የተጠመቁ ምእመናን ወዲያዉ ሜሮን ሲቀቡ መንፈስ ቅዱስ ያድርባቸዋል።

ካህኑ የተጠመቀዉን ሰዉ ወይም የተጠመቀችዉን ሴት ሜሮን የሚቀባላቸዉ የሰዉነት ክፍሎች በመጽሐፈ ክርስትና ላይ ተመልክተዋል። ካህኑ የተጠመቀዉን ሰዉ ሜሮን ከቀባ በኋላ እጁን በራሱ ላይ ይጭንበታል፤ ማለት በተጠመቀዉ ሰዉ ራስ ላይ እጁን ያኖራል። ከዚያም የተጠመቀዉ ሰዉ ወንድ ከሆነ በካህኑ ቃል የክርስትና አባት ቀርቦ ይቀበለዋል። ሴት ከሆነች ደግሞ የክርስትና እናት ቀርባ ትቀበላታለች።

ተጠምቀዉ ሜሮን ከተቀበሉ በኋላ ያጠመቃቸዉ ቄስ እጁን በራሳቸዉ ላይ መጫን (ማኖር) እንደሚገባዉ በመጽሐፈ ክርስትና ተደንግጎአል።

## ጥያቄ- የክርስትና አባት ወይም እናት አገልግሎት ምንድን ነዉ?

የክርስትና አባትና እናት ለተጠመቁት ሰዎች የሃይማኖት ወላጆች ናቸዉ፤ ስለዚህ በጥምቀተ ክርስትና ያነሡአቸዉን የሃይማኖት ልጆቻቸዉ ስለሆኑ በሃይማኖት የማሳደግና ትምህርተ ሃይማኖትን የማስተማር ኀላፊነት አለባቸዉ። ከዚሁ ጋርም የተጠመቀዉን ወንድ ልጅ የክርስትና አባት ሆኖ ሊያነሳዉ የሚችል ወንድ ሲሆን፣ የተጠመቀችዉን ሴት ልጅ ደግሞ የክርስትና እናት ሆና የምታነሳት ሴት መሆን እንዳለባት የቤተክርስቲያን ሕገ ቀኖና ያዛል።

ተጠምቀዉ ሜሮን የተቀበሉ አዲስ አማንያን ወዲያዉኑ በዚያኑ ዕለት ምንም ሳይቀምሱ ቅዱስ ቁርባን መቀበል እንደሚገባቸዉ ቤተክርስቲያናችን ታዛለች። ተጠምቀዉና ቅብዓ ሜሮን ተቀብተዉ ቅዱስ ቁርባን ሳይቀበሉ መመለስ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያናችን ሕግ አይደለም፤ ስለዚህ ወዲያዉ መቁረብ ይገባቸዋል።

## ጥያቄ- ማጥመቅ፣ ሜሮን መቀባትና ማቁረብ የሚችል ማን ነዉ?

ማጥመቅ፣ ሜሮን መቀባትና ማቁረብ የሚችል በአንብሮተ እድ የተሾመ ሥልጣነ ክህነት ያለዉ ነዉ።

ከትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት 1991 አቡነ ገብርኤል ከጻፉት የተወሰደ።